## ዶ/ር ታዬ ወ/ሰማያት የአንጋፋው ኢመማ  ፕሬዝዳንት

## የኢትዮጵያ ሲቪክ ማኀበራት  የጋራ መድረክን በመወከል በመላው ዓለም ለሚገኙ ኢትዮጵያውያን ያስተላለፉት መልዕክት

የተከበራችሁ ኢትዮጵያውያን ወገኖቼ!
ክቡራትና ክቡራን!

በአንድ ፓርቲ ፈላጭ ቆራጭነት ተቀፍድዶ የቆየው የኢትዮጵያ ፖለቲካ ወደ መድብለ ፓርቲ ሥርዓትና ውድድር መሸጋገሩን ያበሰረው የግንቦት 7 ምርጫ በሕብረተሰባችን ሙሉ ተሳትፎ ተካሂዷል፡፡ በሕዝብ ፈቃድና ይሁንታ የተመሠረተ ኢትዮጵያዊ መንግሥት ዕውን ለማድረግ በመላ ሀገሪቱ የተካሄደው ይህ ዲሞራሲያዊ እንቅስቃሴ እጅግ ውድ የሆነውን የሕይወት መስዋዕትነትም አስከፍሎአል፡፡

በዚህ ታሪካዊ ምርጫ ሕዝቡ በነቂስ ወጥቶና ከዳር እስከ ዳር ተንቀሳቅሶ ፍጹም ጨዋነት በተላበሰ ሥርዓት ድምፁን የሰጠው፤  በድህነትና የፍትህ እጦት ለዘመናት ስትንገላታ የኖረችው እናት ሀገራችን  ከተውተበተበችበት ኋላ ቀር አስተዳደርና አምባገነን  አገዛዝ ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ትላቀቅ ዘንድ ባደረበት ብሩህ ተስፋና ፅኑ ዕምነት ነው፡፡

ይህ ሕዝባዊ ዕምነትና ተስፋ ከታለመለት ግብ ይደርስ ዘንድ ከሁሉም በፊት የድምፅ ቆጠራው ከማናቸውም ዓይነት የማጭበርበርና የስርቆት ድርጊቶች በፀዳ መልኩ በሐቅ መካሄድና መከበርም ይኖርበታል፡፡

ፍትህ የተጓደለበትና የግፍና አምባገነናዊ አገዛዝ ያንገፈገፈው የኢትዮጵያ ሕዝብ በግንቦት ሰባቱ ምርጫ በሚወስደው ርምጃና በሚሰጠው ውሣኔ ከመንበረ-ሥልጣን እንደሚፈነግላቸው የተገነዘቡት የገዥው ፓርቲ ሹማምንት፤ በምርጫው ዋዜማና በማግስቱ ጭምር እጅግ አሳፋሪና ሕገወጥ ተግባራትን ፈጽመዋል፡፡

በሕዝቡ የማይገሰስና የማይደፈር መብት ላይ አሲረዋል፡፡ የሕዝብ መብትና ፍጹም አንጡራ ሃብት የሆነውን ድምፁን በአስፈጻሚ አካሎቻቸውና በታጠቁ ኃይሎቻቸው አማካኝነት በመንጠቅና በማስነጠቅ ኮሮጆአቸውን የመሙላት ደባ ፈጽመዋል፡፡

የገበሬ አባቴ፣ የገበሬ እናቴ፣ ወንድምና እህቶቼ ድምፅ አይሰረቅ!! በማለት የሕግ ያለህ! የሀገር ያለህ !! ያሉ ወገኖቻችንን ደም በከንቱ አፍስሷል! ሰብዓዊ ርህራሄ በጐደለውና በቀል በተጠናወተው ጭካኔ የተሞላበት ሁኔታ በየእስር ቤቱ በማጐር አስቃይቷል፡፡እያሰቃያቸውም ነው፡፡

ውድ የሃገሬ ልጆች ሆይ!

በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ የተፈጸመውንና ዛሬም ድረስ ያልተገታውን የወያኔ ኢሕአዴግ የሕዝብ ድምፅ ነጠቃም ሆነ በንፁሃን  ዜጐች ላይ ሲፈጸም የቆየውን የማንአለብኝነት ድርጊት በማውገዝ፣  ታይቶም ሆነ ተሰምቶ በማይታወቅ ሃገራዊ ፍቅርና ወገናዊ ስሜት በመነሳሳት በዓለማችን አራቱም ማዕዘናት በማከናወን ላይ ያላችሁት ታሪካዊና ሃገራዊ ግዴታን የመወጣት ተግባር በእጅጉ አኩርቶናል!! አስከብሮናል!!

በኢትዮጵያ ሲቪክ ማኅበራት የጋራ መድረክ እንዲሁም በራሴ ስም አድናቆቴንና ልባዊ ምሥጋናዬን አቀርባለሁ።

ይህ ለሀገራችሁና ለወገናችሁ ያላችሁን ዕውነተኛ ፍቅር የገለጻችሁበት፣ ታሪካዊና በተለይም የዜግነት ግዴታችሁን ለመወጣት በማካሄድ ላይ ያላችሁት የሕዝብ ድምፅ የማስከበርና አምባገነኖችን የመፋረድ እንቅስቃሴ፤ ኢትዮጵያ ለምትገነባው የሰላምና የዲሞክራሲ ሥርዓት  የሚያበረክተው አስተዋጸኦ እጅግ! እጅግ! ከፍተኛ ነው።

ስለዚህም የተነሳሳችሁለት ዓላማ ከግብ ሳይደርስና የሕዝብ የሥልጣን ባለቤትነት ሳይረጋገጥ ግንባራችሁን እንዳታጥፉና ያነገባችሁትን የሰላምና የዲሞክራሲ መፈክር ከእጃችሁ እንዳታወርዱ፣ በድጋሚ በኢትዮጵያ ሲቪክ ማኅበራት ስም ወገናዊ ጥሪዬን አቀርባለሁ።

ውድ የኢትዮጵያ ልጆች ሆይ!

ገዥው ፓርቲ በሕዝብ አንጡራ ሀብት የሚተዳደሩትን  መገናኛ ብዙሃን በፍጹማዊ ቁጥጥሩ ሥር አውሎ የሕዝብን የማወቅና ሃሣቡን በነፃነት የመግለጽ መብት በማፈን በአደንቋሪ   ፕሮፖጋንዳ ለመሸንገል በመራወጥ ላይ ይገኛል። በነፃ ፕሬስ ላይ አምባገነናዊ እጁን በመጫንም ማዋከቡንና በሕግ ሽፋን ጥቃቱን ቀጥሎበታል።

የውጭ የዜና ወኪሎችን በማገድ ሕዝብ አማራጭና ዕውነተኛ ዜና እንዳያገኝ ዕብሪት የተጠናወተው ተግባርም ፈጽሞአል። ስለዚህም ዓለም አቀፉ ሕብረተሰብና የኢትዮጵያ ወዳጆች ሁሉ በሃገርና  በሕዝብ ላይ እየተፈጸመ ያለውን በደልና ዕውነታውን ይገነዘቡት ዘንድ ሁለገብ እንቅስቃሴያችሁን አጠናክራችሁ   ትቀጥሉ ዘንድ የኢትዮጵያ ሲቪክ ማኅበራት ወገናዊ ጥሪያቸውን  ያቀርባሉ!

በመጨረሻም የሃገራችንና የሕልውናችን ዕጣ  በምልዓተ ሕዝቡ፣ ሳይማር ባስተማረንና ከአብራኩ በተከፈልነው ፣  በሀገር ውሰጥና በመላው ዓለም በምንገኘው፣ ሕፃን፣ ወጣት፣ ሴት፤ ወንድ፣ጐልማሳና አዛውንት ዜጐች እጅ ነው።

ታሪክና ትውልድ የጣለብንን አደራ ለመፈጸምና ለማስፈጸም ቃል ኪዳናችንን እናድስ። የሕዝባችንን ድምፅ ላለማስነጠቅ በሕብረትና በፅናት እንቁም!

የሕዝብ ድምፅ ይከበር!!!!

ኢትዮጵያና ሕዝቧ በነፃነታቸው ተከብረው ለዘለዓለም ይኑሩ!!